# የት ይደርሳል የተባለ ጥጃ ልኳንዳ ቤት ተገኘ

## እንደሚባለው

## የት ይደርሳል የተባለ "መደመር" የህዝብ ድጋፍና አመኔታ አጥቶ

## በ4-ወራት መሬት ላይ ዘጭ አለ


ህዳሴ ኢትዮጵያ አስተያየት ያለው በ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com ማድረስ ይቻላል

# የት ይደርሳል የተባለ ጥጃ ልኳንዳ ቤት ተገኘ እንደሚባለው የት ይደርሳል የተባለ "መደመር" የህዝብ ድጋፍና አመኔታ አጥቶ በ4-ወራት መሬት ላይ ዘጭ አለ

## መግብያ

የተከበራቹ ውድ አንባብያን፣ ይህንን ፅሁፍ ለመፃፍ ያነሳሳኝ በአገራችን እየተካሄደ ያለው የመደመር ለውጥ በአገራችን ህዝቦች እንዴት ይታያል በሚል ጥያቄ ባለፉት ሁለት ሳምንታት በፌስቡክ ተከታታዮች ላይ የተደረገ የጥናት ውጤት ነው፡፡ የጥናት ሂደቱ ቀላል እና አንድ ክሊክ ብቻ የሚፈልግ ነው፡፡ ድምፅ አሰጣጡ ገና ያላለቀ እና ቀጣይ ነው፡፡ ግን ደግሞ ባለፉት ሁለት ሳምንታት (ከሓምሌ 24 - ነሓሴ 8፣ 2010 ዓ.ም. ) የተሰጠውን ድምፅ ብቻ መሰረት በማድረግ የወጣውን ሪፖርት *"ለፈው ሳምንት 83% የኢትዮጵያ ህዝብ የጠ/ሚ ዶ/ር አብዪ አሕመድ የለውጥ ሂደት እንዳንገሸገሸው የፌስቡክ የጥናት ውጤት አረጋገጠ"* ይላል ሪፖርቱ አጭር አንድ ገፅ በመሆኑ እንዳለ እንደሚከተለው አቀርበዋሎ

> *መደመር እንዴት ታየዋለህ የሚል ጥያቄ ተጠይቆ ባለፈው ሳምንት ከ604 ድምፅ ሰጪዎች 218 ወይም 36% የመደመር ለውጡን እንደሚደግፉ ሲገልፁ 386 ወይም 64% ደግሞ የመደመር ለውጡ እንደሚቃወሙ ነበር፡፡ በዚህ ሳምንት የድምፅ አሰጣጡ ቀጥሎ ውጤቱ የመደመር ተቋዋሚዎች እየተበራከቱ መሄዱ ያሳያል፡፡ ባለፈው ሳምንት ጥናቱ ከ8384 ሰዎች ተነስቶ 8829 ሰዎች ጋር በመድረሰየ 445 ሰዎች ባለፈው ሳምንት ደርሷል፡፡ ከነዚህ 445 ሰዎች ግን 78 ሰዎች ወይም 17.53% ሰዎች ድምፅ ሰጥቷል፡፡ ይህ ካለፈው ሳምንት የነበረው 7.2% ድምፅ ሰጪ ወደ 17.53% ማደጉ ያሳያል፡፡ ዋናው ነገር ግን ባለፈው ሳምንት ድምፅ ከሰጡት 78 ሰዎች 65 ሰዎች ወይም 83% የመደመር ለውጡ የሚቃወሙ ሲሆን 13 ሰዎች ወይም 17% ብቻ የመደመር ሂደቱ የሚደግፉ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ይህ ሲጠቃለል እስከ ዛሬ ድረስ ጥናቱ ወደ 8829 ሰዎች የደረሰ ሲሆን ከነዚህ*


ህዳሴ ኢትዮጵያ አስተያየት ያለው በ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com ማድረስ ይቻላል

*ውስጥ 682 ሰዎች ወይም 7.72% ብቻ ድምፅ ሰጥቷል፡፡ ከነዚህ ድምፅ የሰጡት 682 ሰዎች ውስጥ 231 ሰዎች ወይም 34% መደመር በጣም ጥሩ ነው እደግፈዋለሁ ሲሉ፣ 451 ሰዎች ወይም 66% ደግሞ መደመር ትክክል አይደለም አልደግፈውም በማለት ድምፃቸው ሰጥቷል፡፡ ይህ የሚያሳየው ከጊዜ ወደ ጊዜ መደመር እና ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ እየተጠሉና ቦታ እያጡ እንደሆን ባለፉት ሁለት ሳምንታት የተሰጠው የህዝብ አስተያየት ያሳያል፡፡ ለዚህም ምክንያት ይሆናል ተብሎ የሚገመተው በሶማሌ ክልል የነበረው የሰላም እጦት፣ በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች እየታዩ ያሉ ያለመረጋጋትና በየቀኑ እርስበርሳቸው የሚጣረሱ መግለጫዎች፣ ትዕይንቶች፣ ወዘተ ህዝቡ መደመርን እንዲጠላና እንዳይደግፈው አድርጎታል የሚል እምነት አለ፡፡ ትናንት በሻሸመኔ የተፈፀመው አስነዋሪ ድርጊት ደግሞ ህዝቡ በበለጠ የመደመር ሂደቱ እንዲጠላ የሚያደርግ እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ስለዚ አሁንም ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ ጊዜ ሳይሰጡ የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ ሰብስቦ የለውጡ ሂደት በሰከነ መንፈስ በመገምገም ለውጡን የህዝብ ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ እንዲመሩት ይጠበቃል፡፡ አለበለዚያ አደጋው በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ዳሰሳው ገና ተጨማሪ ሳምንታት ያሉት በመሆኑ የፌስቡክ ተጠቃሚዎች በሚከተለው ሊንክ በመጫን ድምፅ መስጠት እንደሚቻል ለመግለፅ እወዳለሁ፡፡*

[https://m.facebook.com/story.php?story_fbid=2133413950033961&id=1537115639663798](https://m.facebook.com/story.php?story_fbid=2133413950033961&id=1537115639663798)

*ሲስተሙ ድምፅ ለሰጠ ብቻ ውጤቱ ይታያል፣ ፕሮግሬሱም በየጊዜው እያዩት ይሄዳሉ፡፡ ድምፅ ያልሰጠ ግን ውጤት ማየት አይችልም፡፡*

*ከሀዳሴ ኢትዮጵያ፣ ይላል፡፡*

ይህ ታድያ ለምን ሆነ? ጠ/ሚ ዶ/ር አብዩ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገርም ከፍተኛ ድጋፍ እንዳላቸው ይታወቃል ከመቼ ጀምሮ ነው ይህ የህዝብ ድጋፍ ማሽቆልቆል የጀመረው? የሚሉ ጥያቄዎች ለመመለስ እና ጥናቱን ከቁጥር በዘለለ ወደ መሬት ለማስነካት "የት ይደርሳል የተባለ ጥጃ ልኳንዳ ቤት ተገኘ" በሚል ርእስ ይህን ትንታኔ አቀርባለሁ፡፡

## መልካም ንባብ


ሀዳሴ ኢትዮጵያ አስተያየት ያለው በ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com ማድረስ ይቻላል

# የት ይደርሳል የተባለ ጥጃ ልኳንዳ ቤት ተገኘ እንደሚባለው የት ይደርሳል የተባለ "መደመር" የህዝብ ድጋፍና አመኔታ አጥቶ በ4-ወራት መሬት ላይ ዘጭ አለ

ጠቅላይ ሚንስትር ዶ/ር አብዪ መጀመሪያ ስልጣን ሲይዙ በሁሉም አከባቢ በሶሻል ሚድያ በተደረገው ጥናይ፤ በኢቲቪ እንደተገለፀው ከ90% በላይ ህዝብ ድጋፉ እንደገለፀ ይነገር ነበር፡፡ የቁጥሩ መጠን አከራካሪ ቢሆንም አብዛኛው ህዝብ ድጋፍ እንደነበረው አያከራክርም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ የተጀመረውን የህዳሴ ጉዞ ሳይሰናከል፣ ግለቱን ጠብቆ እንዲቀጥል ይፈልግ ስለነበር፣ *ለውጡ ከኢህአዴግ ውስጥ ፈልቆ የወጣ ስለነበር የአገሪቱ ህዝቦችና ብሄር ብሄረሰቦች በደስታና በፈንጠዝያ ነበር የተቀበሉት፡፡* አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ምናልባት በትግራይ ክልል እንደ ሌላው የአገሪቱ ክፍል ድጋፍ አያገኙም ይሆናል የሚል መላምቶች ያቀርቡ የነበረ ቢሆንም፣ በዛን ሶሞን በርካታ የትግራይ ተወላጆች ድጋፋቸውን ይሰጡ ነበር፡፡ ለምሳሌ ጠ/ሚንስተሩ ወደ መቐለ ከመምጣታቸው በፊት የድምፅ ወያነ ትግራይ ድ.ወ.ት. በፌስቡክ ገፁ ባደረገው ጥናት ከ65% የማያንስ በዶ/ር አብይ ሃሳብና ንግግር ተማርኮ ሲደግፍ 35% የሚቃወም ነበር፡፡ ጠ/ሚንስትሩ መቐለ ከተማ ተገኝተው ለከተማው ነዋሪ በትግርኛ ባደረጉት ንግግር፣ በተለይ ህዝቡ ሊያነሳቸው ይችላል ብለው አስቀድመው በማወቅ የነበሩትን ብዥታዎች በሚያጠራ መልኩ ማብራርያ በመስጠታቸው እና በሰጡት የሰላምና የመልማት ተስፋ፣ ሰማእታት የሰጧቸውን አደራና መስመሩ እንደ ቀድመው እቦታው እንዳለ ሲገልፁና ቃል ሲገቡ ህዝቡ በታላቅ ደስታ ነበር የተቀበለው፡፡

የጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር አብይ አሕመድ በመጀመሪያዎቹ ጉብኝቶቻቸው ህዝብን ሲያነጋግሩ *ስለ ፍቅር፣ ስለ አንድነት፣ ስለ መቻቻል፣ ስለ ይቅርታ፣*

<u>*ስለ ምሕረት*</u> ሲሰብኩ ሁሉም በቴሌቪዥን መስኮት እንዲከታተላቸው ይፈልግ ነበር፡፡ በእርግጥም በመጀመሪያዎቹ እርምጃዎች እስረኞች መፍታት ሲጀምሩ፣ የይቅርታና የምሕረት አሰራርና ሕጎች ሲያወጡ፣ በየጎረቤት አገሮች ሂደው የታሰሩ ዜጎቻችን ሲያስፈቱ፤ አገራችን በውጭ ምንዛሪ እጥረት አደጋላይ በመግባቷ ይህን ችግር ለመፍታት ከወዳጅ አገሮች ያመጡት መፍትሄና በአገር ውስጥ በባለሃብቶች ከባንክ ውጭ ተከማችቶ የነበረ የውጭ ምንዛሬ ወደ ባንክ እንዲገባ ማድረጋቸው፤ ባለፉት 27 ዓመታት ኢትዮጵያን የማተራመስ አጀንዳ ይዘው ከተለያዩ የአገራችን መረጋጋት የማይፈልጉ ሀይሎች ግንባር በመፍጠር የሽብር ተግባር ሲፈፅሙ የነበሩ የተለያዩ ድርጅቶች እንደነ ኦነግ፣ ኦብነግ፣ ግንቦት 7፣ አርበኞች ግንባር፣ የኦጋዴን ነፃአውጪ ወዘተ የትጥቅ ትግል ትተው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ይዘው ለመታገል በመወሰን ወደ አገርቤት መግባታቸው፤ ዶ/ር አብይ አሕመድ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል አድናቆት የተቸራቸውና ልክ እንደ የእግዚአብሄር ልዑክ ተደርገው ነበር የተወሰዱት፡፡

በተለይ ከኤርትራ መንግስት ጋር ያደረጉት የሰላም በር አከፋፈት በጣም በጣም የሚደነቁበት ተግባር ነበር፡፡ ኢትዮ ኤርትራ ጦርነት እንደሚታወቀው በ21ኛው ክፍለዘመን ከፍተኛ የሰው ህይወት የቀጠፈ የወንድማማቾች ጦርነት እንደነበር ለማንም ግልፅ ነው፡፡ እንዲህ በደም የተቀባባ ጥላቻ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በመወነጃጀል እና አንዱን ለሌላው ለማጥፋት ሴራ የሚያሴርበት ግንኙነት በአጭር ጊዜ ሰላም ይወርዳል ብሎ ማሰብ በማይቻልበት ጊዜ ዶ/ር አብይ ተአምር ሰርቷል፡፡ የአለማችን ታሪክ እንደሚያሳየው በእንደዚህ አይነት ከፍተኛ እልቂት የታጀበ ጥላቻ የሰፈነባቸው ጎረቤታሞች፣ ሰላም ማውረድ የሚቻለው <u>***ቢያንስ ያሉት መሪዎች በአንድ ወይም ሁለት ትውልድ ሲተካካ ነው፡፡***</u> የኮሪያዎች የሰላም ድርድር ቢታይም ያው ብዙ መሪዎች የተተካኩ

ቢሆንም ገና አጥጋቢ ሰላም አልወረደም፡፡ የኛ ጉዳይ ሲታይ ግን በኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ኤርትራ (በተለይ ደግሞ መሪዋ ኢሳያስ አፈወርቂ) ጠባጫሪ በተባለችበትና አሁንም በስልጣን ላይ ያለበት ሁኔታ፤ ኤርትራ ሌት ተቀን ኢትዮጵያን ለማፈራረስ በምትጥርበት ወቅት፣ ኢትዮጵያም የኤርትራ መንግስት ጠባጫሪነት ተግባራት በአለም ደረጃ እንዲጋለጥ በማድረግ ተደራራቢ ማዕቀቦች እንዲጣሉላት ያደረገች፣ የኢትዮጵያ ጠ/ሚ ብድግ ብሎ ያለ 3ኛ ወገን አደራዳሪ ኤርትራ ገብቶ ሰላም ማረጋገጥ፣ በተለይ የፕሬዚዳንት ኢሳያስ ልብ መማረክ እውነትም በማንም ተደርጎ የማያውቅ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ የህዝቡን ልብ የማረኩና በጠ/ሚ ዶ/ር አብይ ከፍተኛ ተስፋ እንዲኖር ያደረጉ ፍፃሜዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከጠ/ሚ አፍ ግራ የሚያጋቡ ንግግርም ይደመጡ ነበር፡፡ ለምሳሌ የተከበሩ ጠ/ሚ ዶ/ር አብዪ አሕመድ ***ባለፉት 27 ዓመታት የጨለማ አመታት እንደ ነበሩ፤*** ***ኢህአዴግ ለራሱ አሸባሪ ድርጅት ሆኖ እያለ*** ለሌሎች ድርጅቶች አሸባሪ እያለ ያስር እንደነበር በአደባባይ ሲገልፁ፤ በተሰብሳቢዎች ከፍተኛ ጭብጨባና ሞራል ሲቸራቸው ነበር፡፡ ነገርግን ከአዳራሹ ውጭ፣ ወይም ከተሰብሳቢው ውጭ ሆኖ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ይከታተል የነበረው ህዝብ ግን የተደበላለቀ ስሜት፣ መደናገጥ፣ መደናገር በመፈጠሩ ራሱ በራሱ፣ እርስ በርሱ መጠየቅ፣ መጠያየቅ፣ መከራከር ጀመረ፡፡

አብዛኛው በቅን ልቦና ***"እንዴ ባለፉት 27 ዓመታት በኢህአዴግ መሪነት ጨለማ ላይ ነው እንዴ የነበርነው?"*** የሚል በውስጡ ሲያመላልስ ነበር፡፡

ይህም ከፍተኛ መነጋገሪያ ሆኖ የሰነበተ ሲሆን፤ ወጣቱ አዛውንቱ ሁሉ ባለፉት 27 ዓመታት የተፈፀሙ ፍፃሜዎች በማሰብ በማውጣትና በማውረድ የየራሱ ድምዳሜ ሰጥቷል፡፡ እኔም ለግንዛቤ ይሆን ዘንድ ትንሽ ጠቀስ ላድርግ፡፡

ባለፉት 27 ዓመታት ኢህአዴግ በኢትዮጵያ አገራችንና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያመጣው ለውጥ ሲመዘን ምን ያህል ነው? የሚለው ጥያቄ ለመመለስ ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመምጣቱ በፊት የነበረውን ሁኔታ ማየት የግድ ይላል፡፡ ምክንያቱ የኢህአዴግ ለውጥ ለማየት ኢህአዴግ ምን ተረከበ፣ ኢህአዴግ ምን አስረከበ የሚል በማየት ልዩነቱ በቀላል ማወቅ ስለሚቻል፡፡

## *በፖለቲካው በኩል*

የመንግስት ሃይማኖትና የመንግስት ብሄር ተለይቶ በህግ የተቀመጠባት፣ በስመ የአንድነት ስጋት በሚል ፈሊጥ ቋንቋ፣ ብሄር፣ የተለያዩ እምነቶች፣ ባህሎች፣ ህልውናቸው የተካዱባት፣ የመንግስት አገልግሎት ለማግኘት የግድ የአማራ ማንነት ተላብሶ መምጣት /ቋንቋው፣ ባህሉ፣ ወጉ/ የህዝቦች የእኩልነት መብቶች በአደባባይ በህግ ተረግጠው፣ ከአማራው ብሄር ውጭ ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በብሄራዊ ጭቆና ሲማቀቁ፣ ከተዋህዶ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ውጪ ያሉ ሃይማኖቶች የእምነት ነፃነት አጥተው ሲሰቃዩ፣ የእምነት ቦታዎች ሲከለከሉ፣ ነበር ኢህአዴግ አገርን የተረከባት፡፡

ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በፍፁም የማይታወቅባት አገር፣ የሰብኣዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥሰት ተቀባይነት እንዳለው ተደርጎ የሚወሰድባት አገር፣ ሰው በአደባባይ የሚረሸንባትና አስክሬን ለመውሰድ ገንዘብ የሚከፈልባት አገር፣ ሰውን በመግደል ጥይት ስለባከነ የሟች ዘመድ የጥይት ዋጋ የሚከፍልባት በአለማችን ምናልባት ሲኦል የሚባል ካለ አገራችን በቅድሚያ የምትጠቀስ አገር፣ ነበር ኢህአዴግ ኢትዮጵያን የተረከባት፡፡

ይህን ጭቆና የወለደው 17 የታጠቁ ድርጅቶች፣ ኣብዛኞቹ የመነጠል ጥያቄ ያነገቡና ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታን ነፃነት የሚሉ የነበሩ፣ በአጠቃላይ

ኢትዮጵያ ከአንድነቷ ይልቅ መበታተንዋ ጎልቶ የሚታይበት ወቅት ነበር ኢትዮጵያ ኢህአዴግን የተረከባት፡፡

## በኢኮኖሚ በኩል

ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ሲረከባት በኢኮኖሚ ደረጃ የዓለማችን የድሆች ድሃ የሆነች አገር እንደተረከበ፣ የ50 ሚልዮን ህዝብ አገር ኢትዮጵያ በመንግስት ካዝና 32 ሚልዮን ዶላር ብቻ፣ መሰረተ ልማት ነክ በጥቂት ዋና ዋና ከተሞች ብቻ እንጂ ገጠሩ ጠቅላላ መሰረተ ልማት የሚባል ያልነበረበት ትምህርት፣ ጤና፣ መንገድ፣ መብራት፣ ስልክ፣ ወዘተ የማይታሰብበት ሁኔታ ነበር፡፡ በአጠቃላይ የአገራችን ኤኮኖሚ ከዓለም ጭራ መሆን ብቻ ሳይሆን ዕድገቱ በፍጥነት የሚያሽቆለቁልበት ነበር፡፡

## ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ከተረከበባት ጊዜ ጀምሮ ምን ለውጥ አመጣ

ለውጡ ለመደርደር ጊዜም ቦታም የለም የፅሁፉ ዓላማም አይደለም ነገር ግን ልዩነቱ ለማየት ያክል ትንሽ ልጥቀስ

## በፖለቲካው በኩል

ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረና በህዝብ ምርጫ ይሁንታ አግኝቶ ኢትዮጵያን በመራቸው 27 ዓመታት በፖለቲካው በኩል መሰረታዊና ተአምራዊ ለውጥ አስመስግቧል፡፡ ያደጉ አገሮች አሁን የደረሱበትን የዴሞክራሲ ስርዓት ለመገንባት ከ200 ዓመት በላይ የፈጃቸው ሲሆን ኢህአዴግ ግን አገራችን ከጨለማው/ሲኦል አውጥቶ እዚህ ለመድረስ 27 ዓመታት ነው የፈጀው፡፡ አሁን የመንግስት ሃይማኖትና የመንግስት ብሄር የሚባል ነገር የለም መንግስትና ሃይማኖት በህግ የተለያዩ ናቸው፡፡ ሁሉም

ብሄር ብሄረሰቦች ከአማራ ጋር እኩል መብት አላቸው እኩል ተደማጭነት አላቸው፤ የወፍ ቋንቋ ይባሉ የነበሩ ሁሉም ቋንቋዎች ሺ.ተናጋሪ ያለውም ሚልዮኖች ተናጋሪ ያላቸውም ሁሉም ከአማርኛ ጋር እኩል የመነገር፣ የመደመጥ፣ የመጠቀም መብት ኣላቸው በአጠቃላይ አሁን የበላይና የበታች፣ የሚባል ብሄርና ቋንቋ የለም፣ ቤተኛና ቤተኛ ያልሆነ ወይም አንደኛና ሁለተኛ ዜጋ የሚባል የለም ሁሉም እኩል ናቸው፡፡

ከእኩልነትም ባለፈ ሁሉም በራሱ ጉዳይ ራሱ የሚወስንበት ራሱ በራሱ የሚተዳደርበት፣ ክልሉ የሚያለማበት፣ ባህሉ ቋንቋው የሚያሳድግበት፣ በቋንቋው የሚማርበትና የሚዳኝበት ዕድል ተፈጥሯል፡፡ ሁሉም በጋራ ጉዳዮች፣ አገራዊ ጉዳዮች እኩል ተደማጭና ፍላጎቱን የመግለፅ መብቱ ተጎናፅፏል፡፡

የነዚህ ሁሉ መብቶች፣ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ዋስና የሆነውን በሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች ይሁንታ የፀደቀ የህዝባዊ፣ ዘመናዊና ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግስት ባለቤት ለሞሆን የበቃነው በኢህአዴግ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ዴሞክራሲያዊ አንድነቷ አስጠብቃ፣ በመቻቻልና በመከባበር እነሆ ያለ ጦርነት 27 ዓመት በኢህአዴግ ዘልቃለች፡፡

## ***<u>በኢኮኖሚ በኩል</u>***

ኢህአዴግ የተረከባትን በፍጥነት ረጅም የሏልዮሽ ጉዞ ስትጓዝ የነበረችው አገር ኢትዮጵያ፣ ***<u>የሏላ ማርሽ በመቀየር የፊተኛው ማርሽ በማስገባት</u>*** በአሁኑ ሰዓት ማንም የሚመሰክረው ከዓለማችን በፈጣን የኤኮኖሚ ዕድገት ከሚጠቀሱት አገሮች አንዷ ለመሆን በቅታለች፡፡ ይህ ዕድገት ተራ የቁጥር ድርደራ ሳይሆን በትክክል በአገሪቱ ያለውን የመሰረተ ልማት፣


ህዳሴ ኢትዮጵያ አስተያየት ያለው በ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com ማድረስ ይቻላል

የኢንቨስትመንት አውታሮች፣ የትምህርትና ስልጠና ተቋሞች የጤና ተቋሞች፣ የመንገድ ዝርጋታ፣ የውሃ አቅርቦቶች ወዘተርፈ በማየት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይህ ዕድገት ፍትሃዊነቱን ሲታይ ደግሞ በፍትሃዊነታቸው የሚጠቀሱ የዓለማችን አገሮች አንዱን ያደርጋታል፡፡ ምክንያቱም የመሰረተ ልማት ዝርጋታ በመሰረቱ የሚገነባው በመንግስት በመሆኑና የዚህም ዋናው ተጠቃሚው ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በመሆኑ የሃብት ክፍፍሉ ፍትሃዊነት ማረጋገጫ ነው፡፡ የፕሮጀክቶች ድልደላና ምደባ በዋናነት በባጀት አወሳሰን የሚወሰን በመሆኑ፣ እዚህ ላይም 60% ለህዝብ ብዛት መሰረት ያደረገ ክፍፍል 25% ለሗላ ቀር ክልሎች ማበረታቻ የሚሰጥ በመሆኑ የሃብት ክፍፍሉ ፍትሃዊነት ማረጋገጫ ነው፡፡ በአጠቃላይ የልማቱ ደረጃ፣ የህዝቡ ተሳትፎና ተጠቃሚነት በተጨባጭ የተረጋገጠ መሆኑ የሚያሳየው አንዱ ማሳያ አማካይ የሰው የመኖር ዕድሜ Life Expectancy ከ45 ጀምሮ በኢህአዴግ 64 ዓመት መድረሱ በአለም አቀፍ የገንዘብና የልማት ተቋማት ያወጡት ሪፖርት ማየቱ በቂ ይመስለኛል፡፡

## ባለፉት 27 ዓመታት የነበሩ ችግሮች

አገራችን ኢትዮጵያ በኢህአዴግ መሪነት ፈጣን ቀጣይነት ያለውና ፍትሃዊ ***ልማት ሲረጋገጥ መንገዱ አልጋ-ባልጋ አልነበረም፡፡*** እንደየ አከባቢው፣ እንደየ ክልሉ፣ እንደየ ንቃተ-ህሊናው በርካታ ችግሮች አጋጥመው ችግሮቹ በመፍታት ነው እዚህ ደረጃ የተደረሰው፡፡ ***ዋናው ችግር የመልካም አስተዳደር እና የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮች ናቸው፡፡*** እነዚህ ችግሮችም ያ የምንገነባው የካፒታሊስት ስርዓት ባህርያዊ ችግሮች ናቸው፡፡ ይቅርና እኛ በነፃ ገበያ ገና ዳዴ በማለት ላይ የምንገኝ ባደጉ የሚባሉ አገሮችም እነዚህ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ ነገር ግን ለበርካታ አስርት ዓመታት የገነቡት የዴሞክራሲና የነፃ ገበያ ስርዓት በመሆኑ፣ ስርዓቱ እንደ ባህል፣ ልምድ ተደርጎ ስለተገነባ


ህዳሴ ኢትዮጵያ አስተያየት ያለው በ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com ማድረስ ይቻላል

እነዚህ ችግሮች የሚፀየፍ ህብረተሰብ ፈጥሯል፣ ስለሆነም እነዚህ ችግሮች ለነሱ አሳሳቢ አይደሉም እንጂ ጠቅላላ የሉም ማለት አይደለም፡፡

በኛ ጉዳይ ጀማሪዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ እየገነባነው ያለው ስርዓት ገና ባህልና ልምድ አልሆነም፣ ***ችግሮችን የሚጠየፍ ህብረተሰብ አልፈጠርንም፣ ችግሮችን ከመቅረፍና የመፍትሄ አካል ከመሆን ይልቅ በአቋራጭ መንገድ መሄድ የሚመርጥ ሕብረተሰብ እና ለዚህ ኣቋራጭ መንገድ የሚመች ሁኔታ ነው ያለው፡***፡ አመራሩም ኣባሉም እንደድሮው የትጥቅ ትግሉ ጊዜ ሂይወቱን ለዓላማው ለመሰዋት የቆረጠ ኣይደለም፣ ብዙ የሚሻሙ ነገሮች አሉ፣ ቤተሰብ፣ ልጅ፣ የራስ ብቃትን ማሻሻል ወዘተ ተሻሚ ነገሮች ተፈጥሯል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ነገሮችም ሙሉ በሙሉ ለዓላማው እንዳይቆም ጊዜውንና ተነሳሽነቱን ይሻሙታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እድገቱ እየተፋጠነ፣ ልማቱ ሁሉም ጋ እየደረሰ በሄደ ቁጥር የሁሉም ፍላጎት እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ለምሳሌ አንድን ዓይነት መሰረተ ልማት በአንድ አከባቢ ብትዘረጋ ብቻውን ትርጉም የለዉም፣ መሰረተ ልማቶች እርስ በራሳቸው የተሳሰሩ ናቸው፣ ተሳስረውም ነው ውጤት የሚመጣው፡፡ በገጠር ቀበሌ መንገድ ዘርግተህ መኪና/አምቡላንስ ከሌለ ጥቅሙ ውሱን ነው የሚሆነው፡፡ ካልተሟሉ ደግሞ ትልቅ የመልካም አስተዳደር ጉዳይ ይሆናል፣ ህዝቡ ያማርራል፡፡ መብራት ዘርግተህ መቆራረጥ ካጋጠመ ይህም ትልቅ የመልካም ኣስተዳደር ችግር ከመሆን አይቀርም፡፡

መሰረተ ልማቶች አሟልተህም ብቃት የሌለው ሲቪል ሰርቫንትና ቢሮክራሲ ካለም ይህም የመልካም ኣስተዳደር ችግር ሆኖ ቁጭ ይላል፡፡ በመልካም አስተዳደር እና በህዝቡ የአገልግሎት እርካታ የሲቪል ሰርቫንቱና የአመራሩ ሙያዊ ብቃትና ህዝባዊ የአገልጋይነት ኣመለካከትም ደረጃ ቁልፍ ሚና አለው፡፡ ***ከአገልጋይነት በመውጣት የያዙትን የመንግስት ሃላፊነት ለግል ጥቅም ማዋል፣ ጉቦና ክፍያ መጠየቅ፣ ወዘተ ቀንደኛ የመልካም አስተዳደር***

ችግሮች ናቸው፡፡ እነዚህን ሁሉ ልክ የልማቱ ደረጃ የሚመጥን ግንባታ ለውጥ ካልመጣ የፈለገው ልማት ቢረጋገጥ የህዝቡን እርካታ ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በኢህአዴግ የታየውም ይህ ነው፡፡ እነዚህ ዓይነት ችግሮች ሁሌም የሚያጋጥሙና በየጊዜው እየተከታተሉ መፍታት ፋቱን መድሃኒት ቢሆንም፤ ባለፉት 15 ዓመታት ግን ችግሮችን የመፍታት ወኔ እየተዳከመ በመምጣቱ እዚህ አሁን ካለንበት አደገኛ ጊዜ ደርሰናል፡፡ ችግሮች ሲያጋጥሙ በየጊዜው ህዝቡ ምሬቱ ይገልፅ የነበረ ቢሆንም የሚሰጡ የነበሩ መፍትሄዎች የእሳት ማጥፍያ መፍትሄ እንጂ መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጣ መፍትሄ አልነበረም፡፡ ለዚህ ነው ባለፉት 3 ዓመታት ኢህአዴግ ከግምገማና ከተሃድሶ ሳይላቀቅ፣ ታጥቦ ጭቃ እየሆነ በስተመጨረሻ ስርዓቱን ማስቀጠል አቅቶት እነሆ አገራችን በቄሮዎች፣ ፋኖዎችና ሄጎዎች ስር ወድቃ ዜጎቻችን የሕገ-መንግስት ያለ፣ የመንግስት ያለ፣ የፀጥታ አስከባሪ ያለ እያሉ በየቀኑ የዜጎች እሪታና ዋይዋይታ መስማት ሆነ፡፡ በዚህ ጊዜ ነው ለውጥ አረጋግጫለሁ የሚል የመደመር ሀይል ብቅ ያለው፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት 27 ዓመታት የለውጥና የህዳሴ ጉዞ ሲገመገም በተለይ አገራችን ከነበረችበት ሁኔታ በመነሳት እላይ እንደተዘረዘረው ሲታይ በጣም ትልቅ ለውጥ የተመዘገበበትና ሕብረተሰቡም ተጠቃሚ ያደረገ ብዙዎች ድሃ አገሮች የኛን አካሄድ እንደ ሞዴል ለመውሰድ የሚሯሯጡበት፣ የዓለም ባንክ፣ የዓለም የገንዘብ ድርጅትና ሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለተሞክሮ እስከ መቀመር ያደረሰ የህዳሴ ጉዞ ነው ተብሎ ይወሰዳል፡፡

*ታድያ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ እንዴት 27 ዓመት የጨለማ ጉዞ ነበር ይላሉ? የግል ጥቅም ስለጎደለባቸው ይሆን?*

- ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ በዚች አገር ከማንም በላይ የስርዓቱ ተጠቃሚ እና አመራር የነበሩ ናቸው፡፡ ጠ/ሚ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው፣ የመጀመሪያ፣ የሁለተኛና የሶስተኛ ደረጃ ዲግሪያቸው ያገኙት በአመራር ደረጃ ሆኖው በሚሊታሪና በሲቪል ስራ የህዝብ አገልግሎት እየሰጡ በዚህ ስርዓት ነው፡፡ ስለዚ እንደ ግለሰብ ባለፉት 27 ዓመታት የጠቅላይ ሚኒስተሩ ህይወት በጨለማ ሳይሆን በተሳካ የዕድገት ጉዞ ነው የነበረው፡፡ ስለዚ በግላቸው ጥቅም ስለጎደላቸው አይደለም ያለፉት 27 ዓመታት የጨለማ ጉዞ ነበር ያሉት፤

## ታድያ ለምን? በትክክል ልማት ስላልነበረ ነው?

- የልማቱም የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታም ቢሆን ቅድም ለመግለፅ እንደ ሞከርኩት ባለፉት 27 ዓመታት የኢህአዴግ የለውጥ እና የህዳሴ ጉዞ በጣም በጣም ውጤታማ ነበር፡፡ በዓለማችን በጣም ፈጣንና ውጤታማ የልማት ጉዞ ነበራቸው የሚባሉት የሩቅ ምስራቅ አገራት ነበሩ፡፡ እነሱም በ40 እና በ50 ዓመታት ወደ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ተርታ በመሰለፋቸው ነው፡፡ የኛ የኢህአዴግ ጉዞም ከነሱ በመቅደት እነሱ ያላካተቱት እኛ ግን ከብዙሃነታችን የመነጨ የዴሞክራሲ ሌለመንት በመጨመር ከፍተኛ ውጤት እያስመዘገብን በ15 ዓመት በማንም ያልተመዘገበ ውጤት ኢህአዴግ አስመዝግቧል፡፡ ይህንንም ጠ/ሚ በደንብ ያውቁታል በየ ስልጠና መድረክ ሲናገሩት የነበረ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ ራሳቸው በተሳተፉበት የዓለም የሰላም ማስከበር ስራ ኢትዮጵያ ፊት ከሚጠሩት አገሮች ለመሆን የበቃች ናት፡፡ ኢትዮጵያ በልማቱ ጎዳና ያስመዘገበቻቸው ውጤቶች እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የምንመሰክረው ብዙ የአለም አቀፍ ድርጅቶች ይመሰክራሉ፡፡ የኤርትራን ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂን ጨምሮ የውጭ አገራት እንግዶች ሲመጡ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ ራሳቸው የሚያጎበኟዋቸው ያለፉት 27 ዓመታት የተሰሩ ስራዎች ናቸው፡፡ እንዲያውን አንድ ጊዜ ስለ ጉብኝት ሲናገሩ መቐለ እንዴት እንዳደገች ለፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ላሳየው ፈልጌ ነበር ግን .... ማለታቸው የአገራችን ዕድገት ማየት ተስኗቸዋል ለማለት ይከብዳል፡፡ ስለዚህ ከዚህ

በመነሳትም ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ ያለፉት 27 አመታት የጨለማና የቆሻሻ ጊዜ ነው ሊሉት አይችሉም፡፡

## ***ታድያ ኬት በመነሳት ነው ጠ/ሚንስትሩ ወደዚህ ድምዳሜ የደረሱት?***

- በቅን ልቦና በማሰብ የጠቅላይ ሚንስትሩ ድምዳሜ የሕብረተሰቡን ፍላጎት በመረዳት፣ የመጣውን ለውጥ በበለጠ ለማስቀጠል እና ከተረጋገጠው ልማት እና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በላይ ለማስመዝገብ ካለው ፍላጎት በመነሳት እንዲህ /የጨለማና የቆሻሻ ጊዜ ነበር/ ማለት ይቻላል፡፡ መነሻህን ሳታይ መድረሻህን በማየት፣ የህዝብን ፍላጎት በመገንዘብ፣ የህዝቡን ችግርና ሰቆቃ የራስን አድርጎ በመውሰድ በጣም ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ለመቅረፍ ካለው ቀና ፍላጎት በመነጨ ወደዚህ ዓይነት ድምዳሜ አይደረስም አይባልም፡፡
- በርካታ የፖለቲካ ተንታኞችና ታዛቢዎች በጠ/ሚ ዶ/ር አብይ ንግግር ብዙ ደስ ያላላቸው ሂስ ሲያደርጓቸው፤ አብዛህኛው ህዝብ በአዎንታ ነበር ያየውም የወሰደውም፡፡ ምክንያቱ ህዝቡ ባለፉት 5-7 ዓመታት በምርጫም በተለያዩ መድረኮችም የኢህአዴግ መስመር ወይም የህዳሴ ጉዞ ያመጣቸው ለውጦች እውቅና በመስጠት ግን ደግሞ በአፈፃፀም ላይ ይስተዋሉ የነበሩ ችግሮችን ይገልፅ ስለነበር፣ ***ዶ/ር አብይ አሕመድም የኢህአዴግ ሊቀመንበር ከመሆናቸው በፊትም ቢሆን የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር በመሆናቸው የህዝቡን ልብ ትርታ ይረዳሉ ብሎ በማሰብ፤*** ጠቅላይ ሚንስትሩ የተጀመረውንና በመቀዛቀዝ ላይ ያለውን የህዳሴ ጉዞ በማነቃቃት ከተመዘገበው በላይ ለማስመዝገብና ታሪክ ለመስራት ስለፈለጉ ነው የሚል ነበር ህዝቡ የወሰደው፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ ቀን በቀን እየተተካ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ህዝቡ ከጠ/ሚ ***የሚጠብቀው ነገር ሌላ*** - ***ቃላትና ንግግር ሌላ*** - ***ተግባር እና ተጨባጭ ሁኔታ ሌላ*** ወይም የማይገናኙ ሲሆኑ፣ ድብብቆሽ ሲበራከቱ ህዝቡ ራሱን መጠየቅ ጀመረ፣

የት ይደርሳል የተባለ ጥጃ እንደተባለው የመደመር ሀይሉ በመሸወድ /በድብቅ ሴራ/ እንደመጣ ሁሉ ተስፋ የተደረገበትን ለውጥ ማምጣት ይቅር የነበረውም ማስቀጠል የማይችል የባሰ የጥገኛ ሀይል ሆኖ ቁጭ አለ፡፡ ይቅርና የዴሞክራሲ የነፃነት ለውጦች ሊያመጡ፣ ሚድያዎች ሁሉ በቀላጤ ደብዳቤ በማዘዝ ከመደመር ውጭ ሌላ እንዳይዘገብ፣ የህዝቡ እሮሮ እንዳይሰማ፣ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች መፈናቀል እንዲደበቅ፤ ሕገ-መንግስት ባለበት አገር በአደባባይ የብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች መብት የሚረግጡ፣ የሚያንቋሽሹ መፈክሮች ይዞ መውጣት፤ የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት የሚያረጋግጥ የፌደራላዊ ስርዓታችን ሰንደቅ ዓላማ በአደባባይ መቅደድ፣ ህዝብን እንደ ህዝብ መስደብ ማንቋሸሽ፣ የመደመር ሂደቱ ገና አንድ እርምጃ ሳይጀመር ብሄር ብሄረሰቦች መቀነስ ጀመረ፡፡

ይህ እንዲህ እያለ ጠ/ሚ ዶ/አብዪ በጥርጣሬ ዓይን እንዲታዩ ያደረጋቸው ብዙ የአፍ ወለምታዎች እና ሻጥሮች ወይም ተንኮሎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው በተለይ በትግራይ ህዝብ ዘንድ ጥርጣሬ ያስገባው ነገር ህወሓትና የትግራይ ህዝብን ለመነጠል ያደረጉት ንግግር ነበር፡፡ ዶ/ር አብዪ የኦህዴድ ታጋይ የነበሩ በመሆናቸው ከማንም በላይ በትግራይ ህዝብና በድርጅቱ ህወሓት ያለውን ግንኙነት በደንብ ያውቃሉ የሚል እምነት በሁሉም የትግራይ ተወላጅ አለ፡፡ በእርግጥ በኢህአዴግ ያጋጠመው የዝቅጠት ችግር የመስመር ወይም የፕሮግራም ችግር እንዳልሆነና የሰዎች /መሪዎች/ ችግር እንደሆነ፣ መስመሩ ዘመን ተሻጋሪ እንደሆነ፤ በትግራይ ህዝብና በህወሓት ያለውን ግንኙነት ከተራ የምርጫ ፖለቲካ በላይ በደምና በከባድ መስዋእትነት የተሳሰረ እንደሆነ፣ የሚታወቅ ነው ነገር ግን ጠ/ሚ ይህን ግንኙነት ማጣጣላቸው ማንም አልወደደላቸውም፤

የኢ.ህአዴግና የኢ.ትዮጵያ ህዝብ ባለዉለታዎች የሆኑትን የኢ.ህአዴግ ነባር አመራሮች፣ ከነበራቸው የመንግስት ስራ በአልማሚት በአንድ መስመር ፅሁፍ ለውለታቸው በማይመጥን ማሰናበት፣ ከዚህም አልፎ እንዲህ አደረግናቸው ብሎ መደነፋት ሆደ ሰፊው ህዝብ አልወደደላቸውም፤ በኢ.ትዮጵያውያን ባህል ታላላቆቹ የማያከብር ማንም አያከብረውም፡፡ ራሱ በራሱ የተዋረደ ነው፡፡ ከሁሉም የባሰ ደግሞ ተጨባጭ ማስረጃ ሳይዙ በአደባባይ የቀን ጅቦች ብሎ መሰየም፣ በእርግጠኝነት እሳቸው በኪራይ ሰብሳቢዎች መከበባቸው በደንብ ያውቁታል፡፡ በኢ.ህአዴግ የትግል ታሪክ ኪራይ ሰብሳቢነት እንደ መታገያ እንጂ እንደ ማስፈራሪያ አይወሰድም፤ ጠ/ሚ ግን ኪራይ ሰብሳቢነት እንደ ማስፈራሪያ በመጠቀም የተለያዩ ስም በማውጣት ከመሪ የማይጠበቅ ንግግር ማድረግ፤

በኢ.ህአዴግ የዝቅጠት ችግር ሲገመገም የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር የሁሉም አባል ድርጅቶች ችግር እንደሆነ እንጂ የአንድ ድርጅት እንዳልሆነ፤ የትግራይ የበላይነት፣ የህወሓት የበላይነት የሚል ፕሮፖጋንዳም ተገምግሞ የተሳሳተና በተለይ በእህት ድርጅቶች ያለ አመራር ከህዝብ ጥያቄ ማምለጫ የሚጠቀምበት እንደሆነ፤ በዳግም ጥልቅ ተሃድሶ ህወሓት በጥሩ ሁኔታ በመገምገም በከፍተኛ አመራሩ የወሰደውን እርምጃ በማድነቅ ሁሉም የኢ.ህአዴግ አባል ድርጅቶች የህወሓትን አርአያ በመከተል ዳግም ጥልቅ ተሃድሶው እንዲያካሂዱት የሚል እንደ ስራአስፈፃሚ ገምግሞ ሲያበቃ፣ የኢ.ህአዴግ ሊቀመንበር ዶ/ር አብይ አሕመድ ግን አንድ ድርጅት ላይ ያነጣጠረ የቀን ጅብ የሚል ስም በማውጣት ማሸማቀቅ፤

ዶ/ር አብዩ ከኢ.ህአዴግ አመራር ውጭ ሆኖው የመጡ ይመስል በየመድረኩ እኛ አንሰርቅም፣ እኛ ስርቅ የምንፀየፍ ነን፣ ወዘተ ሲሉ .... እንዴ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አሕመድ ኢ.ህአዴግ አይደል እንዴ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የጠ/ሚ

ወንበር የሰጣቸው? ምነው ጠቅላይ ሚንስተሩ በመንግስት ግልበጣ ነው እንዴ ስልጣን የያዙ? ሕገ-መንግስት ከሚፈቅደው ውጭ ስልጣን በመፈንቅለ መንግስት ሲያዝ ህግ አስከባሪ የለም እንዴ? እስከ ማለት ደርሷል፡፡

ኢህአዴግ ሲገመግም የትግራይ ወይም የህወሓት የበላይነት የሚለው ፕሮፖጋንዳ ሆን ተብሎ በትግራይ ህዝብና በሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ማሀከል ክፍተትና መቃቃር ለመፍጠር እንጂ ውሸት ነው ብሎ ሲያበቃ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ ወደ ስልጣን ከመጡ ቦኋላ የትግራይ ተወላጆች ከፌደራል እና ከአዲስ አበባ የመንግስት መዋቅር የማፅዳት ዘመቻ በስፋት ተያያዙት፡፡ የየድርጅታቸው ኪራይ ሰብሳቢ በጓያቸው ስር ወሽቀው መቐለ የሌቦች መናሀርያ የሚል ስም ሲያወጡ የትግራይ ህዝብ "ምእንቲ እዛ መጎጎ ትሕለፍ እዛ አንጭዋ" በማለት በትዕግስት ሲያልፍ ቄሮ እና ፋኖ የሚል ስም የወጣላቸው ነውጠኛ ቡድን፣ የመሪዎቹ ንግግር እየተከተለ ብሄር ተኮር ጥቃቱን አጧጧፉት፡፡

በኢህአዴግ ውስጥ ኢህአዴግ የማያውቀው አንድ ቡድን በማቋቋም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እምነት አለው የተባለውን እና መደመር ይቃወማል ተብሎ የሚታሰብን በማትኮር ኪራይ ሰብሳቢነትን ከመታገል ፋንታ ኪራይ ሰብሳቢነትን የሚታገል ሰበብ አስባብ እየፈጠሩ ማደን፣ የራስን ጉድፍ ትተህ በሌሎች ድርጅቶች እጅ መቀሰር፣

ለምሳሌ በደቡብ የተፈጠረው ግጭት እና ስርዓት አልበኝነት እንደ መነሻነት በመውሰድ በደኢህዴን ውስጥ ስጋት ይሆኑናል የተባሉትን በማስፈራራት ከስልጣን እንዲወርዱ ማድረግና ድርጅቱን ማፈራረስ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በአማራና በኦሮሚያ ክልል ተመሳሳይ ግጭትና ስርዓት አልበኝነት ሲፈፀሙ

አይቶ እንዳላየ ማለፍ፣ በሚድያ እንዳይተላለፍ ማድረግ፤ ባጭሩ ዓይን ያወጣ አድልዎ መፈፀም ዕለታዊ ተግባር ሆኖዋል፡፡

በተለይ የዶ/ር አብዪ ጠቅላላ አካሄድ ***ግልፅነት የሌለው የድብብቆሽ ጨዋታው*** ደግሞ የበለጠ ***ስጋት እንዲነግስ አድርጓል***

- ድብቅ ተልእኮ ያላቸው የፌደራል ፖሊስ እና የመከላከያ ሰራዊት መለዮ በማልበስ እስከ አፍንጫቸው የታጠቁ ሰራዊት ከክልሎች እውቅና ውጭ በአውሮፕላንም በመሬትም በማስገባት በክልሎች ስጋትና አለመተማመን መፍጠር፤
  - እንደዚህ ዓይነት ስውር ዓላማ ይዞ ወደ መቐለ የተሰማራው ሀይል በህዝቡና የክልሉ የፀጥታ ሀይል ንቁ ተሳትፎ ሲከሽፍ፤
  - በኢትዮ-ሶማሌ ክልል በተመሳሳይ የተሰማራው ሃይል ግን ከቁጥጥር ውጭ በመሆኑ፣ በጅግጂጋ ለተፈጠረው ውድመትና እልቂት ሰበብ ሆኖዋል፤ ጥቁር ጠባሳ የተወ አስነዋሪ ክስተት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኖዋል
- በሌሎች ክልሎችም በተመሳሳይ መልኩ ማንነታቸው የማይታወቅ ፀጉረ ለወጥ ታጣቂዎች ሲሰማሩ ይስተዋላሉ፡፡
- በዴሞክራሲያዊ የህዝብ ምርጫ ወደ ስልጣን የመጡትን ዜጎች በቀላጤ ደብዳቤ የስልጣን መልቀቂያ እንዲያስገቡ ማስፈራራት፣
- በጠቅላላ በኢህአዴግ ታሪክ ውስጥ ***የኢህአዴግ አሰራር በመጣስ በምትኩ ድብቅ ቡድን በማደራጀት ትላልቅ አገራዊ ጉዳይ በጥቂት የኦህዴድና ብአዴን አመራር ብቻ እየተማከለ የጥፋት መንገድ መጓዝ የሚጠቀሱ ናቸው***፡፡ ይህ ድብቅ ዓላማ ያለው ቡድን ህዝቡ ምንም የማያውቅ ይመስለዋል፣ ቡድኑ ብቻ ኣዋቂ፣ የሚሰራው የሚያቅደው ሴራ ምሽጥር የሆነ ይመስለዋል፤ በዘመነ ኢንፎርሜሽን ያለን መሆኑ የዘነጋ አጥፊ ቡድን ነው፡፡

የኢትዮ ኤርትራ ሰላም ጉዳይ በሚመለከት ህዝብ ለህዝብ የሚደረግ ግንኙነት ሲጠየቅ የመንደር ፖለቲካ ማለቱና በኢሳያስ በኩልም ጌም-ኦቨር የሚሉ ሲደማመር ይኼነገር የሰላም ነው በሚል በጥርጣሬ እንዲታይ አድርጓል፡፡

የዚህ ሁሉ የድብብቆሽና የተንኮለ እንቅስቃሴ ውጤት አገሪቷ ወደ ባሰ አለመረጋጋት እንድትገባና የብሄር ተኮር ግጭት እንዲባባስ፣ ስርዓት አልበኝነት እንዲነግስ፣ በጠራራ ፀሃይ የዜጎች ንብረት መዘረፍ፣ ማቃጠል ሆኖዋል፡፡

አሁን ባለንበት ስልጡን ዘመን፣ የተለያዩ አመለካከቶች ነፃ እና ግልፅ በሆነ መንገድ ለህብረተሰቡ ቀርበው ሕብረተሰቡ ይሆነኛል የሚለውን፣ የመሰለውን ነፃ ሆኖ ያለምንም ጫና የፈለገውን የሚመርጥበት የዴሞክራሲ ዘመን ላይ፣ በዓለም ላይ የሌለ ነገር መደመር በሚል ፈሊጥ የጨዋታ ህግ የሌለው ፀረዴሞክራሲ ተግባራት ሲፈፀሙ እና የዜጎች ሕገመንግስታዊ መብቶች ሲጣሱ ህግ አስከባሪ ታጥቶ ህዝብ ሲሰቃይ ይታያል፡፡

የት ይደርሳል የተባለ ጥጃ ልኳንዳ ቤት ተገኘ እንዲሉ የት ይደርሳል የተባለ መደመር

- መልካም አመለካከት ያለው እና መጥፎ አመለካከት ያለው፣
- ጥሮ ግሮ መክበር የሚፈልግ እና ቀምቶ፣ ሰርቆና ገድሎ መክበር የሚፈልግ፣
- ዴሞክራሲ፣ ነፃ የሃሳብ መንሸራሸርና የህዝብ ወሳኝነት የሚፈልግ እና ፀረዴሞክራሲ፣ አፈናና እኔ አውቅልህ አሎህ ባይ፣
- እኔ እገነጠላሎ የሚል እና አይ የኔ ጥቅም ዴሞክራሲያዊ አንድነት ሲረጋገጥ ነው የሚል
- በአጠቃላይ ፖዚቲቭ (+) እና ነጋቲቭ (-) በመደመር እልቂት፣ አለመረጋጋት፣ የሃብትና ንብረት ውድመት፣ የመንፈስ መረበሽ እና


ሀዳሴ ኢትዮጵያ አስተያየት ያለው በ hidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com ማድረስ ይቻላል

ስጋት፣ የሃይማኖቶች ግጭት፣ የብሄሮች ጥላቻ፣ ወልዶ አገራችን ከፍተኛ የስጋት ዳመና አንዣብብዋት ይገኛል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ሕብረተሰቡ ልክ መጀመሪያ በራሱ ጊዜ "መደመርን" እንደደገፈ ሁሉ፤ እላይ በተዘረዘሩት ምክንያት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ እምነት አጥቶ፣ ተስፋው እየጨለመበት በመሄዱ ማማረር ጀምሯል፡፡ ሕብረተሰቡ እየተቋወመ ያለው ፍቅር፣ ይቅርታ፣ ምሕረት፣ አንድነት አይደለም፡፡ ህዝቡ እየተቃወመ ያለው መደመር ተከትሎ የመጣው የሰላምና መረጋጋት እጦት ነው፡፡

የአገሪቱ ህግ በአደባባይ በመድፈር የጨዋታው ህግ ሕገ-መንግስት መሆኑ ቀርቶ በመደመር ተተክቶ የተደመሩት ፖዚቲቭ (+) እና ነጋቲቭ (-) ውጤታቸው መቀነስ ሆኖ እነሆ ባለፉት የጠ/ሚ ዶ/ር አብዩ አሕመድ ጥቂት የስልጣን ወራት ኢትዮጵያችን በርካታ ዜጎችዋ ተቀንሰውባታል፣ ብዙ ሽማግሌዎች፣ ሴቶችና ህፃናት ሂይወታቸውን አጥቷል፣ ተፈናቅሏል፣ ብርቅየ ባለሞያችን (ኢንጂኔር ስመኘው በቀለ) አጥተናል፣ እግዚአብሄር አወጣቸው እንጂ ጠቅላይ ሚንስተራችንም ራሳቸው በደመሯቸው ሀይሎች ሰኔ 16፣ 2010 ዓ.ም. አጥተናቸው ነበር፡፡ ሰላምና መረጋጋት እየጠፉ ስርዓት አልበኝነት ታይቶ በማያውቅ መልኩ ተባብሳል፡፡ ቄሮና ፋኖ ዝርፍያ ግድያ ላይ ተሰማርቷል፡ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ እና ደጋፊዎች ከመደመር ምርቃናና ሆይሆይ ገና አልነቁም፤ ይህን ሁሉ ኪሳራና ጥፋት በፍፁም ሊታያቸው አልተቻለም ወይም ሊያይዋቸው አልፈለጉም፡፡

ሚድያዎቻችን የጋዜጠኝነትን ስነምግባር በመጣስ ጋዜጠኞቻችን በግላዊ ስሜቶቻቸው በመገዛት ትክክለኛው መረጃ ማቅረብ ትተውታል፣ **የህዝቡ ሚድያ ፌስቡክ እየሆነ መጥቷል፡፡ ፌስቡክ ደግሞ ልክ እንደ "መደመር" የጨዋታ ህግ የሌለው ማንም እንደፈለገ የሚፈነጭበት በመሆኑ የብጥብጥና**

**ዓመፅ መቀስቀሻ ሆኖ፣ በሬ ወለደ ወሬዎችና ፎቶግራፎችን በመለጠፍ ቀንደኛ የብሄር ተኮር ጥቃት ማዘዣ ሆኖዋል፡፡**

***"መደመር"*** ህዝቡ አሁን እያንገሸገሸው ነው፡፡ በሶማሌ ክልል ላይ የፌዴራሉ አያያዝ ችግር አለበት፣ በሀይል የሚሆን ነገር የለም ዘመኑ የመከባበር ነው፡፡ ኢትዮጵያ አንድን ወገን ስለፈለጋት ብቻ አንድነቷን ይጠበቃል ማለት አይደለም፡ ሁሉም የሚኳኳላት ስትሆን ብቻ ነው ጠንካራ አንድነት የሚኖረው፡ ፡ ይህም የሚሆነው በመከባበርና በመቻቻል ነው፡፡ ህገመንግስቱ በማክበርና እንዲከበር በማድረግ ብቻ ነው፡፡ ጠ/ሚ እየተከተሉት ያለ አግላይ ፖለቲካ የምንወዳት አገራችን እንዳናጣት የስፈራል፡፡ ስለዚህ ጠ/ሚንስተራችን ተረጋግተው ቢመሩን፡፡ የሚናገሩት ነገር ከአፋቸው ከማውጣታቸው በፊት ሁለቴ ሳይሆን *__አስር ጊዜ በማሰብ ቢናገሩ__*፡፡ የሁሉም ኢትዮጵያዊ መሪ እስከሆኑ ድረስ፣ ሁሉንም ማስደሰት ካልቻሉ ቢያንስ አንድን ቡድን ለማስደሰት አንድን ህዝብ አያስከፉ፡፡

ከህዳሴ ኢትዮጵያ
ነሓሴ 10፣ 2010 ዓ.ም.
አስተያየት ያለው በhidaseethiopia@yahoo.com ወይም hidaseethiopiaa@gmail.com ማድረስ ይቻላል